**የሶማሌና ኦሮሚያ ክልሎች ሕዝበ ውሳኔ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በምርጫ ህጉ አንቀጽ 27 የተለያዩ የምርጫ አይነቶችን እንደሚያካሂድ ይደነግጋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የህዝበ ውሳኔ ነው፡፡ ይህም ሕዝቦች ፍላጐታቸውን ወይም ፍቃዳቸውን የሚገልፁበት አሠራር እና የሕዝብ ፍላጐት በመለካት አስፈላጊውን ውሣኔ ለመስጠት የሚረዳ እንደሆነ በተሻሻለው የምርጫ ሕግ 532/97 አንቀጽ 32 መሠረት ተደንግጓል፡፡

በዚህም መሰረት ቦርዱ ለህዝበ ውሳኔው መልስ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በህዝበ ውሳኔው አፈጻጸም ማብራሪያና የጊዜ ሰሌዳ ላይ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብአት ወስዷል፡፡በመቀጠልም በጊዜ ሰሌዳ ላይ አስፈላጊውን ግብአቶች በማካተትና በማጽደቅ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡

**ህዝበ ውሳኔ ህግ ማዕቀፍ-**

**አንቀጽ 32- 532/99**

1. በህገ መንግሥቱ መሠረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የህዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምጽ የሚስጥበት ስርአት ነው፡፡
2. ህዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ የሚወስነው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ቦርዱ ህዝበዉሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ህዝበ ውሳኔውን ያከናውናል፡፡
3. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

በዚሁ አዋጅ መሰረት ለህዝበ ውሳኔ ድምጽ ሰጪነት የሚያስፈልጉት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**በመራችጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች**

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ/የሆነች፣
- በኦሮሞና በሶማሌ ክልል ስር በሚገኙ ወረዳዎች እናቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆነ/የሆነች
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 አመት እና ከዚያ በላይ የሆነ/የሆነች፣
- በቀበሌው 6 ወር የኖረ/የኖረች ናቸው፡፡
- የህዝበ ውሳኔ ተመዝጋቢው በመደበኛነት ነዋሪ መሆኑን እና ማንነቱን የሚያሳይ ሰነድ በማቅረብ መመዝገብ ይችላል ፡፡
- አስፈጻሚዎች የተመዝጋቢውን ነዋሪነት ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

**በድምፅ ሰጪነት ሊመዘገቡ የማይችሉ**

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያልሆነ/ያልሆነች፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ/የሆነች እና በድምፅ መስጫ ጣቢያው ከ6 ወር በታች የኖረ/የኖረች፣
- በአእምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው/የሌላት መሆኑ ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠበት/የተረጋገጠባት ሰው
- የመምረጥ መብቱ/መብቷ በህግ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሰረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበበት/የተገደበባት ሰው ናቸው፡፡

**የህዝበ ውሳኔው**

የኦሮሚያና የሱማሌ ክልሎች ወሰን ላይ በሚገኙ በ463 ቀበሌዎች የሚኖሩ ሕዝቦች በመረጡት ክልል እንዲተዳደሩ ለሚካሄደው የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም የመራጮች ምዝገባ በአብዛኛው በወጣው የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ በምርጫ ሕጉ እና በአፈፃፀም ሥነሥርዓት መሠረት ተከናዉኗል፡፡

**ህዝበ ውሳኔ ቅድመ ዝግጅት**

የቦርዱ ጽ/ቤት ስለሕዝበ ውሳኔው ሕጋዊ መሠረት፣ ስለሕዝበ ውሳኔ ዓላማና ግብ፣ በሕዝበ ውሳኔው ድምፅ ለመስጠት መመዝገብ ስለሚችሉ ሰዎች፣ ስለሕዝበ ውሳኔው ድምፅ አሰጣጥ ሂደት፣ ስለሕዝበ ውሳኔ አስፈፃሚዎች፣ ስለድምፅ ሰጪዎች፣ ስለኦሮሚያና ስለሱማሌ ክልሎች የቀበሌና የወረዳ የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ወኪሎች፣ ስለነዋሪው ሕዝብ የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ታዛቢዎች እና ስለሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት አስከባሪዎች አመራረጥ፣ ተግባር እና ኃላፊነት እንዲሁም በአጠቃላይ ስለሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም በዝርዝር የሚያስረዳ የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት አዘጋጅቷል፡፡

ይህንኑ ሥነ-ሥርዓት በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በሱማልኛ ቋንቋዎች በበቂ አትሞ በወቅቱ ለሚመለከታቸው አስፈፃሚዎችና ወኪሎች እንዲሁም ለሕዝብ ታዛቢዎች አሰራጭቷል፡፡

ከዚህም በላይ ይኸው ሥነ ሥርዓት በሬድዮ ፋና በሦስቱም ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በሱማልኛ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት ለሕዝቡ በተደጋጋሚ ተገቢውን ገንዛቤ እንዲያስጨብጥ በልዩ ዝግሀደት ተሰራጭቷል፡፡

**የጊዜ ሰሌዳ**

የድምጽ መስጫ ዕለት ጥቅምት 14 ቀን 1997 ዓ.ም ሲሆን ከጥዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ የመራጭነት ካርድ የወሰደ መራጭ ሰላማዊ እና በተረጋጋ ሁኔታ ድምጽ መስጠት ይችላል፡፡

**ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች**

በቅድመ ህዝበ ውሳኔ ዝግጅት በቦርዱ ባለሞያዎች የመስክ ጥናት አካሂደው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን መረጃ አደራጅተዋል። በዚህም መሰረት የኦሮሚያና የሱማሌ ክልሎች ወሰን ላይ በሚገኙ በ463 ቀበሌዎች የሚኖሩ ሕዝቦች በመረጡት ክልል እንዲተዳደሩ ለሚካሄደው የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም የመራጮች ምዝገባ በአብዛኛው በወጣው የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ በምርጫ ሕጉ እና በአፈፃፀም ሥነሥርዓት መሠረት ተከናዉኗል። ይኼም ኤረር ዎረዳ በሚገኙ በ 6 ቀበሌዎች፣ በጉርጉቱ ወረዳ በሚገኙ 2 ቀበሌዎች፣ በባሌ ወረዳ የሚገኙ 31 ቀበሌዎች፣ በጂጂጋ ወረዳ በ 84 ቀበሌዎች፣ በጉርሱም ወረዳ በ78 ቀበሌዎች፣ በሊበን ወረዳ በ 19 ቀበሌዎች፣ በጉላኦዳ ወረዳ በ 18 ቀበሌዎች፣ በ መዩሙሉቄ ወረዳ በ 14 ቀበሌዎች፣ በጉራዳሞሌ ወረዳ በ 14 ቀበሌዎች፣ እና በበርበሬ ወረዳ በሚገኙ 14 ቀበሌዎች ተከናዉኗል።

**የህዝበ ውሳኔ ወኪሎች አመዳደብ (ወረዳ እና ቀበሌ)**

የኦሮሚያና የሱማሌ ክልሎች በየቀበሌዎቹ አንድ አንድ እንዲሁም በየወረዳው አንድ አንድ የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ወኪሎች በደብዳቤ እንዲመድቡ ቀደም ብሎ በቦርዱ ጽሕፈት ቤት ለሁለቱም ክልሎች መስተዳድሮች በደብዳቤ በጠየቀው መሠረት በወቅቱ ተመድበዋል።

የሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓትም በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በሱማልኛ የታተመው አንዳንድ ቅጂ ለወረዳና ለቀበሌ ወኪሎቹ በወቅቱ እንዲደርሳቸው እና ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል።

**የሕዝብ ታዛቢዎችና ሥነ ሥርዓት አስከባሪዎች ምርጫ**

በየቀበሌዎቹ ሦስት ሦስት የነዋሪው ሕዝብ የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ታዛቢዎችና ሦስት ሦስት ሥነ-ሥርዓት አስከባሪዎች በየቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ አማካይነት በወቅቱ እንዲመረጡ ተደርጓል።

ከዚህም በላይ ለነዋሪው ሕዝብና ለታዛቢዎቹ እንዲሁም ለሥነሥርዓት አስከባሪዎቹ ስለሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም በወቅቱ በዝርዝር ማብራሪያ ተሰጥቷል።

**የውጤት መግለጫ ዝርዝር**

| መረጃው ዓይነት | ቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| ድምፅ ለመስጠት የተመዘገበ ሕዝብ ብዛት | 240,526 | |
| ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር | 199,760 | 83.1% |
| ድምጽ ያልሰጡ መራጮች ቁጥር | 41,260 | 17.2% |
| ከድምጽ ሰጭዎች ዉስጥ ወደ ኦሮሚያ ክልል ለመተዳደር (ኦዳ) ድምፅ የሰጠ ጠ/ብዛት | 129,424 | 64.8% |
| ከድምጽ ሰጭዎች ዉስጥ ወደ ሶማሌ ክልል ለመተዳደር (ግመል) ድምፅ የሰጠ ጠ/ብዛት | 70,336 | 35.2% |
| የተሰረዘ ድምጽ | | |
| ዋጋ አልባ ድምጽ መስጫ ወረቀት | | |

የኦሮሚያና የሱማሌ ክልሎች ወሰን ላይ በሚገኙ በ463 ቀበሌዎች ምርጫ ለማካሄድ ታስቦ የነበረ ቢሆንም ባጋጠሙ በተለያዩ ምክኒያቶች በ39 ቀበሌዎች ላይ የሕዝበ ውሣኔው ድምፅ አሰጣጥ ያልተካሄደ እና በሁለት ቀበሌዎች ላይ ድምፅ አሰጣጡ ቢካሄድም ሕገወጥ ድርጊት በመፈፀሙ ውጤቱ በቦርዱ ውድቅ ተደርጓል:: በተጨማሪም በቀሪዎቹ በ422 ቀበሌዎች ላይ ሕዝበ ውሣኔው በምርጫ ሕጉ መሠረት የተከናወን ቢሆንም ከላይ ያለው ሰንጠረዥ ግን በበርበሬ ወረዳ ከተመዘገቡ 14 ቀበሌዎች ዉስጥ የ 4 ቀበሌዎች ዉጤትን አያካትትም::

**የሕዝበ ውሣኔ አፈፃፀም ሂደት እና ያጋጠሙ ችግሮች**

የኦሮሚያና የሱማሌ ክልሎች ወሰን ላይ በሚገኙ በ463 ቀበሌዎች የሚኖሩ ሕዝቦች በመረጡት ክልል እንዲተዳደሩ ለሚካሄደው የሕዝበ ውሳኔ አፈፃፀም የመራጮች ምዝገባ በአብዛኛው በወጣው የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ በምርጫ ሕጉ እና በአፈፃፀም ሥነሥርዓት መሠረት የተከናወኑ ሲሆን

1. **በሞያሌ ወረዳ በሚገኙ 9 ቀበሌዎች ማለትም፡-** ሞያሌ 01፣ ሞያሌ 02፣ ጨሙቅ፣ ቀበናዋ፤ በዴ፣ቡለዲ፣ሞያሌ ኤልጎፍ፣ መደሚጎ እና መለብ የሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም ሂደት ገና ሳይጀመር በሁለቱ ክልሎች የወረዳ እና የቀበሌ ወኪሎች በሕዝብ ታዛቢዎች አመራረጥ፣ በተፈናቃዮች አመዘጋገብ ሁኔታ እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ አለመግባባት

በመፈጠሩ ሁኔታዎች በክልሎቹ ስምምነት መሠረት እስኪመቻቹ ድረስ ሂደቱ እንዲዘገይ ተደርጓል፡፡

2. **በሚኤሶ ወረዳ በሚገኙ 8 ቀበሌዎች ላይ ማለትም፡-**

የሕዝበ ውሳኔ ድምፅ ሰጭዎች ምዝገባ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት በ5 ቀበሌዎች ላይ ከተጠናቀቀ በኋላ

| | |
|---|---|
| በኩርፋ ሰዋ/ኩርፋ ሰዋ ሽንሌ | (482 ድምፅ ሰጪ ከተመዘገበ በኋላ) |
| በገንደ በቀላ/አርማሌ | (403 ድምፅ ሰጪ ከተመዘገበ በኋላ) |
| በገንዳቁሙጠ/ኒኢማሌ | (516 ድምፅ ሰጪ ከተመዘገበ በኋላ) |
| በገንደ ሀርዲም - ሀርዲሞ | (607 ድምፅ ሰጪ ከተመዘገበ በኋላ) |
| በገንዳ በሀቢፍቱ - ሶማዳዩ | (372 ድምፅ ሰጪ ከተመዘገበ በኋላ) |

እንዲሁም ድምፅ ሰጭዎች ምዝገባ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት በ3 ቀበሌዎች ገና ሳይጀመር

| |
|---|
| በገንዳኡፌ/ጉልጀኖ |
| በጎዳሂዳ/ኪቶ/ቲማሪግሌን |
| በገንዳጎልቻ/አቤንሣ |

ሕዝበ ውሳኔ በሚካሄድባቸው በቀበሌዎች ዝርዝር ላይ በሁለቱም ክልሎችና በሕዝበ ውሳኔ አስተባባሪዎች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ማለትም በተለይ በቀበሌዎቹ ስም አቀማመጥ ላይ ወይም በሚለው ምልክት በመለየታቸው በትርጉም መስማማት ባለመቻሉ እንዲቆም ተደርጓል፡፡

3. **በፊቅ ወረዳ የሚገኙ 2 ቀበሌዎች ላይ ማለትም፡-** ሀረሞቲ እና ሲማና መስተዳድሩ የሕዝበ ውሳኔው ሂደት ከመጀመሩ በፊት በወቅቱ ትጥቅ ባለማስፈታቱ የሕዝበ ውሳኔው ሂደት ገና ከጅምሩ እንዲቆም ተደርጓል፡፡
4. **በመዩ ሙሉቄ ወረዳ በ7 ቀበሌዎች ላይ ማለትም፡-** ሐሮሬ ዲቃ፣ሰተዋ፣ ድቢሌ፣ሁርሣ፣ ኡንኩሩሩ፣ሃሮሬሣ ጉዳ እና ነዲ የሕዝበ ውሳኔ አስፈፃሚዎች በየዕለቱ በየተመደቡበት ቀበሌ ላይ ተገኝተው ለድምፅ ሰጭዎች ምዝገባ ዝግጁ ሆነው ቢጠባበቁም ነዋሪዎቹ በወቅቱ በቀበሌዎቹ ላይ ባለመገኘታቸው ምዝገባውን ለማከናወን አልተቻለም፡፡

ይህንኑ ሁኔታ በየዕለቱ በጊዜ ሰሌዳው በተጠቀሱት ቀናት የመራጮች ምዝገባ እስኪጠናቀቅ ድረስ እያዩ ቃለጉባዔ በመያዝ በምዝገባው ላይ እስከመጨረሻው ዕለት ሰው ሊቀርብ እንዳልቻለ አረጋግጠዋል፡፡

5. **በጅጅጋ ወረዳ በ2 ቀበሌዎች ላይ ማለትም፡-** ካረድሌ 1 እና ካረድሌ 2 የኦሮሚያ የወረዳ የሕዝበ ውሳኔ ወኪል ቦታዎቹ ድረስ ከሄደ በኋላ በኦሮሚያ በኩል የይገባኛል ጥያቄው የተነሳ መሆኑን በይፋ በማሳወቁ የሕዝበ ውሳኔው ሂደት እንዳይካሄድ ተደርጓል፡፡

6. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ለቦርዱ ባስተላለፈው የቀበሌዎች ዝርዝር ላይ የአራት ቀበሌዎች ስም በተለያየ ቦታ ተደጋግሞ ተፅፎ በመገኘቱ ቀደም ሲል ለቦርዱ የተላከው ብዛት በአራት ቀበሌ ሊቀንስ ችሏል፡፡

7. በኤረር ወረዳ በኤረር ልዩ ቀበሌ ላይ የመራጮች ምዝገባ እየተካሄደ ሳለ የኦሮሚያ ክልል ወኪሎች ከኤረር ልዩ ቀበሌ ውጪ የሆኑ የዲምቱ፣ የፊቱሌ እና የጎዴ ቀበሌዎች ነዋሪዎች እየተመዘገቡ ናቸው በማለት ተደጋጋሚ አቤቱታ በማቅረባቸው እና ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላም በሶማሌ ክልል ወኪሎች በኤረር ልዩ ቀበሌ ላይ የመራጮች ምዝገባ የተካሄደው ከምርጫ ሕጉ ጋር በሚፃረር መልኩ በመራጭነት ለመመዝገብ ብቁ ያልሆኑ በተለያየ ጊዜያዊ ሥራ ምክንያት ወደአካባቢው የመጡ ሰዎች እንዲመዘገቡ ተደርጓል በሚል በቀረበው ተደጋጋሚ አቤቱታ መሠረት የድምፅ አሰጣጡ ሂደት እንዳይካሄድ ተደርጓል፡፡

8. በጎሮ በቀቅሳ ወረዳ ውስጥ ዳዮ በቀቅሳ ቀበሌ ላይ በሕዝበ ውሳኔው ላይ ድምፅ ለመስጠት በጊዜ ሰሌዳው በተጠቀሱት ቀናት ተመዝጋቢ ቀርቦ ሳይመዘገብ በመቅረቱ ድምፅ ሳይሰጥ ቀርቷል፡ :

9. በጎሮ ወረዳ ለሀርገደብ ቀበሌ ከማዕከል የባርዱ ጽ/ቤት ታሽጎ የተላከው 800 የምዝገባ ካርድ ሲሆን በምዝገባ ወቅት የወረዳው የሕዝበ ውሳኔ አስተባባሪ ለቁሬንሳ ቀበሌ ታሽጐ የተላከውን 1700 የምዝገባ ካርድ አለዋውጦ በመስጠቱ ምክንያት ማጭበርበር ተፈፅሞብናል በሚል በሶማሌ ክልል ወኪሎች በተደጋጋሚ በቀረበው አቤቱታ ተጨባጭነት ሀረገደብ ቀበሌ ላይ 1673 ሕዝብ ቢመዘገብም ድምፅ አሰጣጡ ግን እንዳይካሄድ ተደርጓል፡፡

10. በጎሮ ወረዳ በበቀቅሳ ቀበሌ ላይ የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ በቦታው መካሄድ ሲገባው ምዝገባውን በሀርገደብ ቀበሌ ላይ በተደራቢነት በማካሄዳቸውና ይኸው እንደተደረሰበት ስሕተቱን

ለማረም በተደረገው ጥረት በቀቅሳ ቀበሌ የት ቦታ እንደሆነ እንዲያሳዩ ቢጠየቁም ቦታውን ማሳየት ስላልቻሉ ምዝገባው እንዲቋረጥ ተደርጎ የድምፅ አሰጣጡ ሳይካሄድ ቀርቷል፡፡

11. በምዕራብ ኢሜ ወረዳ በደሎ መንደዩ ቀበሌ የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ሂደቱ ዘግይቶ ቢጀመርም በቅድሚያ የሕዝብ ታዛቢዎች በመመሪያው መሠረት ቢመረጡም ታዛቢዎቹ ኃላፊነታቸውን ትተው በመሄዳቸውና በድጋሚ የቀበሌው ነዋሪ ተጠርቶ የሕዝብ ታዛቢዎች መርጠዉ ምዝገባው ቢቀጥል የሶማሌ ብሔረሰብ ሕዝብ ብቻ በመመዝገቡና በዚህም ላይ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት የሆኑት ተደጋጋሚ ቅሬታ በማቅረባቸው ምዝገባው በወቅቱ ሳይጠናቀቅ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡

12. በሰዊና ወረዳ ቡቃ የተባለው ቀበሌ በወረዳው ውስጥ እንደማይታወቅ የሁለቱም ክልሎች ወኪሎች አረጋግጠው ይህንኑ በመስማማታቸውና በመፈረማቸው የድምፅ ሰጭዎች ምዝገባም ሆነ ድምፅ አሰጣጡ ሳይካሄድ ቀርቷል፡፡

13. በበርበሬ ወረዳ በሌድ ቀበሌ ላይ የሁለቱም ክልሎች ወኪሎችና የጥምር ኮሚቴ አባላት ቀበሌው በወረዳው ውስጥ አለመኖሩን አረጋግጠውና ይህንኑ ተስማምተዉ ስለተፈራረሙ ምዝገባም ድምፅ አሰጣጥም ሳይካሄድ ቀርቷል፡፡

14. በጅጅጋ ወረዳ ጎልማዩ እና ገልቤድ ጅድሌ በተባሉት ሁለት ቀበሌዎች ላይ የቀበሌ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከምርጫ ሕጉና ሥነ ሥርዓቱ ውጪ ድምፅ በማሰጠታቸው ማለትም በጎልማዩ ቀበሌ ላይ ምርጫ አስፈፃሚው መራጮችን እጃቸውን እየያዘ ኦዳ ምልክት ላይ በኦሮሚያ ክልል ምልክት ሲያስደርግ ተደርሶበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በገልቤድ ጅድሌ ቀበሌ ላይ ምርጫ አስፈፃሚው ግመል ምልክት ላይ ለሶማሌ ክልል መራጮችን እጃቸውን እየያዘ ምልክት ሲያስደርግ ተደርሶበታል፡፡

በወቅቱ በሁለቱም ቀበሌዎች ላይ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት እንዲቆም ሲደረግ የሚፈጠረውን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ሁኔታው ለጊዜው እንዲታረም እና የድምፅ አሰጣጡ እንዲቀጥል ተደርጐ ቆጠራው ተከናውኗል፡፡ ከዚያ በኋላ ጉዳዩ በዝርዝር ለቦርዱ ቀርቦ ድርጊቱን የፈፀሙት የምርጫ አስፈፃሚዎች እስከተደረሰባቸው ድረስ ቀደም ሲል ምን ያህል የድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ በዚሁ መልኩ ድምፅ ማሰጠታቸውን ለማወቅ ስለማይቻል ይህም በቀበሌዎቹ የሕዝበ ውሣኔ ውጤት

ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል እና ድርጊቱ ሕገወጥ መሆኑን በማመን ቦርዱ ውጤቱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ በዝርዝር በተገለፁት ምክንያቶች በ39 ቀበሌዎች ላይ የሕዝበ ውሣኔው ድምፅ አሰጣጥ ያልተካሄደ እና በሁለት ቀበሌዎች ላይ ድምፅ አሰጣጡ ቢካሄድም ሕገወጥ ድርጊት በመፈፀሙ ውጤቱ በቦርዱ ውድቅ የተደረገ ሲሆን በቀሪዎቹ በ422 ቀበሌዎች ላይ ግን ሕዝበ ውሣኔው በምርጫ ሕጉ መሠረት መከናወን ቦርዱ አምኖበታል፡፡